

## በእኔ ጎን ያለው ታሪክ መሰማቱን እንዴት ማረጋገጥ እችላለሁ?

- ተባባሪ ይሁኑ እና ተጨማሪ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሰዎችን ስም እና አድራሻ ለጉዳይ ሠራተኛው ያቅርቡ። በአንዳንድ ሁኔታዎች የጽሑፍ ፈቃድ ሊያስፈልግ ይችላል።
- የጉዳይ ሠራተኛው ሁኔታዎን በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ ወደ ቤትዎ እንዲገቡ ይፍቀዱላቸው።
- ስለ ጉዳዩ ወይም ስለ ልጆችዎ ለመነጋገር በሚዘጋጁ ሁሉም ስብሰባዎች ላይ ይገኙ።
- ስለ ሂደቱ እና ምን ማድረግ እንደሚችሉ ጥያቄዎችን ይጠይቁ።
- በተጠየቁ ጊዜ ልጆችዎን ወደ ማናቸውም ቀጠሮዎች ወይም ልዩ ባለሙያዎች መውሰድዎን ያረጋግጡ።
- እንደ አዲስ አድራሻ፣ ቤት ውስጥ የሚኖር አዲስ ሰው ወይም አዲስ የእውቂያ መረጃ ባሉ ማናቸውም ለውጦች ላይ የጉዳይ ሠራተኛው እንደሚያውቅ ያረጋግጡ።
- ስለ ግብዓቶች ይጠይቁ። በአንዳንድ ካውንቲዎች፣ በምርመራው ወቅት እርስዎን ለመርዳት የወላጅ ጠበቆች/ደጋፊዎች ይገኛሉ።
- የጉዳይ ሠራተኛው ስለ ሁኔታው እውቀት ያላቸውን ሌሎች ሰዎች እንዲያውቅ ያድርጉ። የጉዳይ ሠራተኛው የበለጠ መረጃ ባገኙ ቁጥር የተሻለ ውሳኔ ሊያደርጉ ይችላሉ።



## ስለ ጉዳዬ ስጋቶች ቢኖሩኝ ማንን ነው የማናግረው?

ቅሬታ ወይም ስጋት ካለዎት፣ እባክዎ የጉዳይ ሠራተኛዎን ወይም ተቆጣጣሪውን ያነጋግሩ።

____________________________________

____________________________________

ስጋቶችዎ አሁንም ካልተፈቱ፣ ወደ አካባቢዎ አስተዳዳሪ መደወል ይችላሉ።

____________________________________

____________________________________

እርዳታ ለማግኘት በማንኛውም ሰዓት ለህዝባዊ ግንኙነት ቢሮ በ1-800-723-4831 መደወል ይችላሉ

-ወይም-

ለOffice of the Family & Children's Ombuds (የቤተሰብ እና የልጆች እንባ ጠባቂ ቢሮ)* በ1-800-571-7321 በኩል መደወል ይችላሉ።

**ይህ ኤጀንሲ ከDCYF የተለየ ነው። ስለ DCYF የሚኖሩ ስጋቶችን ይመረምራል።*

*የዚህን ሰነድ አማራጭ ቅርጸት ወይም ቋንቋ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎ የDCYF Constituent Relations (የDCYF ህዝባዊ ግንኙነትን) ያነጋግሩ (1-800-723-4831 | 360-902-8060፣ **ConstRelations@dcyf.wa.gov**)።*

DCYF PUBLICATION CWP_0083 AM (08-2021) Amharic

# የChild Protective Services (ሕፃናት ጥበቃ አገልግሎቶች፣ CPS) ምርመራ

### ቤተሰቦችን በሚያጠናክሩበት ጊዜ የልጆችን ደህንነት መጠበቅ



Washington State Department of
CHILDREN, YOUTH & FAMILIES



## የCPS ምርመራ ምንድን ነው?

የCPS ምርመራ አንድ ልጅ ጥቃት እየደረሰበት ነው ወይም ቸላ እየተባለ ነው ለሚለው ክስ ምላሽ ነው። ጥቃት፣ ቸልተኝነት ወይም ፈጽሞ መተው ስለመኖሩ፣ ይህም እንዴት እንደተከሰተ ወይም ልጆችን ለወደፊት ጥቃት ወይም ቸልተኝነት አደጋ ላይ ሊጥል እንደሚችል እና ልጆቹ ደህና ከመሆናቸው ዙሪያ ያለውን እውነታ ለማወቅ ዝርዝር እና ፍትሃዊ ምርመራ ነው። ይህ ከተለያዩ ምንጮች በሚደረጉ ጥያቄዎች እና ቃለመጠይቆች ይጠናቀቃል።

## ለምንድነው ምርመራው የደረሰብኝ?

- Department of Children, Youth, and Families (የሕፃናት፣ ወጣቶች፣ እና የቤተሰቦች ክፍል፣ DCYF) ስለ ልጅችዎ ደህንነት የስጋት ሪፖርት ደርሶታል።
- ሪፖርቱ የልጆች ጥቃት እና ቸልተኝነት ሕጋዊ የሆነውን አተረጓጎም አሟልቷል (RCW 26.44.020)።
- ሪፖርቱ ክሶቹ በመጠኑ ከፍ ያሉ ወይም ከፍተኛ ስጋት ወይም በልጅዎ ላይ ፈጣን አደጋ ሊኖር እንደሚችል አሳይቷል።
- DCYF የልጅዎን ደህንነት ለመጠበቅ ከእርስዎ ጋር መሥራት ይፈልጋል።

## የልጆች ጥቃት እና ቸልተኝነት ፍቺ ምንድን ነው?

የልጆች ጥቃት ወይም ቸልተኝነት ማለት ማንኛውም ሰው በልጁ ጤና፣ ደህንነት ወይም ጥበቃ ላይ ጉዳት መድረሱን ወይም የልጅ ቸልተኛ አያያዝ ወይም እንግልት በሚጠቁሙ ሁኔታዎች ውስጥ በማንኛውም ልጅ ላይ የሚደርስ ጉዳት፣ ወሲባዊ ጥቃት ወይም ወሲባዊ ብዝበዛ ማለት ነው። በመስመር ላይ **https://apps.leg.wa.gov/WAC/default.aspx?cite=110-30&full=true** የሚገኘውን ምዕራፍ 110-30 WACን ለበለጠ መረጃ ይመልከቱ።

## ከምርመራው ምን ሊጠብቁ እንደሚችሉ?

- DCYF የቤተሰብ ክፍልን በእጅጉ ያከብራል እና ልጆች በደህንነታቸው ተጠብቀው መቆየት ከቻሉ በቤታቸው ውስጥ ለማቆየት ይሠራል። የልጅዎ ደህንነት ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ነው እና በተቻለ መጠን ልጅዎን በቤትዎ ውስጥ የሚጠብቁበትን መንገድ ለማግኘት የጉዳይ ሠራተኛው ከእርስዎ ጋር በቅርብ ይሠራል።
- እርስዎ እና ልጆችዎ በማንኛውም ጊዜ በፍትሃዊነት እና በአክብሮት ሊስተናገዱ ይገባል።
- እንደ ወላጅ፣ ሕጋዊ አሳዳጊ ወይም ርዕሰ ጉዳይ የምርመራው አካል ተደርገው ቃለ መጠይቅ ይደረግልዎታል።
- በሕግ፣ እንደ የምርመራው አካል፣ ያለእርስዎ ፍቃድ ልጆች ቃለ መጠይቅ ሊደረግላቸው እና ፎቶዎች ሊነሱ ይችላሉ። ልጆች በቃለ መጠይቁ ወቅት የሚመርጡት ሦስተኛ አካል እዲገኙ የመጠየቅ መብት አላቸው።
- መረጃ መዝገቦችን በማግኘት እና ከተለያዩ አስፈላጊ ግንኙነቶች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ ይሰበሰባል።
- ከክሱ ጋር የተያያዘ የወንጀል አካል ሲኖር፣ የCPS መርማሪው የሚሰበስበውን ተደጋጋሚ መረጃ መጠን ለመቀነስ ከሕግ አስከባሪዎች ጋር በቡድን መልኩ ሊሠራ ይችላል።
- የቤተሰብዎን ፍላጎቶች ለማሟላት፣ የአደጋ እና የደህንነት ስጋቶችን ለመቀነስ፣ ወይም ጉዳይዎ ለክትትል ወደ Family Voluntary Services (ቤተሰብ በጎ ፍቃድ አገልግሎት፣ FVS) ሊዛወር ይችላል።

## ግኝቶች ምንድን ናቸው?

ክሶች "መሠረት አዘል" ወይም "መሠረተ የሌላቸው" ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ። መሠረት አዘል ግኝት ማለት በተገኘው መረጃ መሠረት፣ በልጆች ላይ ጥቃት ወይም ቸልተኝነት የመከሰቱ የበለጠ ዕድል ሲኖረው ማለት ነው። መሠረተ የሌለው ማለት በተገኘው መረጃ መሠረት፣ በልጆች ላይ ጥቃት ወይም ቸልተኝነት ከመፈጸሙ በላይ ያለመፈጸሙ ዕድል ሲበልጥ ወይም ክሱ መፈጸሙን ወይም አለመፈጸሙን ለማረጋገጥ በቂ ማስረጃ ሳይኖር ሲቀር ማለት ነው።

## ስለ ግኝቱ እንዴት ይነገረኛል?

ስለ ግኝቱ የሚገልጽ ደብዳቤ ይላክልዎታል። ግኝቱ መሠረት አዘል ከሆነ፣ ደብዳቤው ግኝቱን እንዴት ይግባኝ እንደሚሉ ይነግርዎታል። ይህ ይግባኝ የግኝት ደብዳቤ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ወደ DCYF ቢሮ መድረስ አለበት አለበለዚያ ግኝቱ የመጨረሻው/ተፈጻሚ ይሆናል። ከተዘዋወሩ የጉዳይ ሠራተኛው አዲሱን አድራሻዎን እንደሚያውቅ እርግጠኛ ይሁኑ።

## መሠረት አዘል ግኝት እኔ ላይ በምን መልኩ ተጽዕኖ ሊያደርስ ይችላል?

መሠረት አዘል ግኝቶች በDCYF የኮምፒውተር ሥርዓት ውስጥ በሚስጥር ይቀመጣሉ። ለሚከተሉት ዓላማዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ:-

- በፍርድ ቤት ውስጥ ስለ ልጆችዎ ድርጊቶች ማስረጃ።
- ለችግር የተጋለጡ ሕጻናትን እና አዋቂዎችን ለመንከባከብ ተቀጥረው፣ ፍቃድ ኖርዎት ወይም ፈቃደኛ ሆነው መሥራት መቻልዎን ለመወሰን።
- የበስተጀርባ/ዳራ መረጃ፣ ወደፊት ሊከሰቱ ለሚችሉ ክሶች።
- ወደ እንክብካቤ ለሚመጣ የዘመድ ወይም የቤተሰብ ልጅን ለማሳደግ ብቁ መሆንዎን ለመወሰን።

